DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

Office of Teaching and Learning

ማዕከላዊ የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድን

# የልዩ ትምህርት (Special Education) አገልግሎቶች፣ በወላጅ-ለተመደቡ የግል-ትምህርት ቤት ተማሪዎች:
# የቤተሰብ መምሪያ (Family Guide)

አዲስና-ማሻሻይ የተደረገበት/Updated: ጃንዋሪ (January) 2026

## ማውጫዎች


ቻይልድ ፋይንድ/Child Find ........ 3
የብቁነት ሂደት ........ 5
ለልዩ ትምህርት (Special Education) እና/ወይም ተዛማጅ- አገልግሎቶች ብቁ-መሆን ........ 6
የሂደቱ - እርምጃዎች/Steps ........ 7
'IEP'ዎች - ከሌላ የአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲዎች/Local Education Agencies (LEAs) ........ 11
ዳግም-ግምገማ (Reevaluation) ........ 13
ፍትሃዊነት ያለው አገልግሎቶች (Equitable Services) ........ 13
ዓመታዊ ስብሰባ ........ 13
የአገልግሎቶች ዕቅድ ........ 13
ፍትሃዊነት(Equitable) ያለው አገልግሎቶች ማግኘት ........ 14

# ቻይልድ ፋይንድ/Child Find

ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ (Individuals with Disabilities Education Act (IDEA)፤ ሃገር-አቀፍ የሆነ ሕግ ሲሆን፣ ብቁ-ለሆኑ ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ልጆች፣ ነፃ ተገቢ-የሆነ የሕዝብ ትምህርት (free appropriate public education (FAPE)ን ማግኘት እንዲችሉ የሚያደርግ ነው። ይህ የሚሆነው፣ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች (special education services)ን ለእነዚህ ተማሪዎች እንዲገኝ-በማድረግ ነው። በ'IDEA' እና በአካባቢው የዲሲ ሕግ/local DC law ስር፤ DCPS - ሁሉንም ከጉዳተኝነት-ጋር የሚገኙ ዕድሜአቸው ከሦስት እስከ አስራ-ሁለት ዓመት የሆኑ በኮሎምብያ ዲስትሪክት ውስጥ ነዋሪ-የሆኑትን - መለየት፣ ማግኘት እና ግምገማ ማድረግ አለበት። ይህ በስራ-ላይ የሚውለው - ለሚከተሉት ነው:

1. የዲሲ ነዋሪዎች ያልሆኑ ልጆች እና፣ በዲሲ ውስጥ በሚገኝ የግል-ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ።
2. የዲሲ ነዋሪዎች የሆኑ ልጆች እና በDCPS ትምህርት ቤት፣ በግል-ትምህርት ቤት፣ ወይም በመኖሪያ-ቤት ማስተማር (homeschool) ውስጥ የሚማሩ

ከ'ቻልድ ፋይንድ/Child Find' ሂደት ጋር ተሳትፎ-ያለው ትክክለኛው-ማነጋገር የሚቻለው ሰው (point of contact) የሚወሰነው፤ በልጃችሁ ዕድሜ እና የሚማርበት ትምህርት ቤት ወይም የልጅ-እንክብካቤ (childcare) የት-ቦታ በመሆኑ-ላይ - መሠረት አድርጎ-ነው።




**የመገኛ አድራሻ:**

'Strong Start' - በ'OSSE ውስጥ

- ስልክ: (202) 727-3665
- መመሪያት/referralን ወደ: [eip.osse.dc.gov](eip.osse.dc.gov) ማስገባት

'ኧርሊ ስቴጅስ (Early Stages)'፣ በDCPS ውስጥ

- ስልክ: (202) 698-8037
- ኢሜል: [info@earlystages.org](mailto:info@earlystages.org).
- መመሪያት/referralን ወደ: [earlystagesdc.org](earlystagesdc.org) ማስገባት

የDCPS ማዕከላዊ የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድን

- ኢሜል: dcps.childfind@k12.dc.gov

- https://dcchildfind.wixsite.com/privateschool

በDCPS ውስጥ - 'ቻይልድ ፋይንድ/Child Find' የሚካሄደው፤ በ'ኧርሊ ስቴጅስ (Early Stages)'፣ በማዕከላዊ የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድን፣ እና በአካባቢ የDCPS ትምህርት ቤት ነው። አንድ-ጊዜ ተማሪዎች ከተለዩ፣ ግምገማ-ከተደረገላቸው፣ እና ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ብቁ-ሆነው ከተገኙ፤ 'አይኢፒ (IEP)'ን እና/ወይም 'የአገልግሎቶች ዕቅድ/Serivces Plan'ን ሊያገኙ-ይችላሉ። ፍትሃዊነት (Equitable) ያለው አገልግሎቶች፣ በዲሲ ውስጥ - በግል ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች - ከአገልግሎቶች ዕቅድ/Services Plan ጋር፣ በማዕከላዊ የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድን ሠራተኞች አማካኝነት የሚቀናበርና-የሚዘጋጅ ይሆናሉ። ተማሪው በአካባቢው/local የDCPS ትምህርት ቤታቸው ውስጥ የሚማር ከሆነ፣ በተማሪው የDCPS ትምህርት ቤቱ አማካኝነት - የ'አይኢፒ (IEP)' አገልግሎቶቹ ይሰጣሉ።

**Who Conducts Child Find at DCPS?**

| | Ages | Location of Students Served | Identifies, Evaluates, and Recommends Services to DC residents | Identifies, Evaluates, and Recommends Services to non-DC residents attending school in DC | Coordinates services through Services Plan | Provides services through IEP |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **Early Stages** | 2 years 8 months - 5 years 10 months | Homeschools and private schools in DC | ✓ | ✓ | | |
| **Central IEP Team** | 5 years 10 months - 21 years | Private schools or Homeschool in DC | ✓ | ✓ | ✓ | |
| **Local DCPS Schools** | 3 years - 21 years | DCPS schools | ✓ | | | ✓ |

## የብቁነት ሂደት

ልጃችሁ - የሆነ-ጉዳተኝነት አለው ብላችሁ የምትጠራጠሩ-ከሆነ፣ የመመራት/referral ጥያቄዎችን ማስገባት ትችላላችሁ። መመራቶች/Referrals፤ በትምህርት ቤትም ሊገባ-ይችላል። መመራቱ/referral፤ ልጁ - ልዩ ትምህርት (special education)ን ለማግኘት ብቁ መሆንና-አለመሆኑን ለመመልከት ያገለግላል። አንድ-ጊዜ መመራቱ/referral ከገባ-በኋላ፤ DCPS - የ'Analyzing Existing Data (AED)'ን ስብሰባ-ለማድረግ - የቀጠሮ-ቀን ለመያዝ ያነጋግራችኋል። የ'AED' ስብሰባው ዓላማ፣ በአሁኑ-ጊዜ ባሉት ስጋቶች-ላይ እና በልጁ የቀለም-ትምህርት የእድገት-ሂደት ላይ ምልከታ-ለማድረግ ነው። ግምገማዎች እንዲደረጉ ሃሳብ-ከቀረበ፤ DCPS - ግምገማ ለማድረግ ስምምነት (consent) እንዲሰጥ ይጠይቃል፤ እና ስምምነት (consent) ከተሰጠ - ከዚያ-በመቀጠል ግምገማዎች ይደረጋሉ። አንድ-ጊዜ ግምገማዎቹ ከተጠናቀቁ-በኋላ፣ ስለ ግምገማዎቹ ውጤቶች ለመወያየት - የብቁነት (eligibility) ስብሰባ ይካሄዳል። ቡድኑ-ከዚያ በመቀጠል፤ ተማሪው - የልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ-መሆኑንና ብቁ-አለመሆኑን ይወስናል። ልጃችሁ - የልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁነትን ካገኘ፣ DCPS - ለልዩ ትምህርት (special education) የመጀመሪያ-አቅርቦት/initial provision - ስምምነት (consent) ለማግኘት-ይጠይቃል። ስምምነቱ (consent) ከተሰጠ፤ በመቀጠል - 'አይ ኢፒ (IEP)' ለማዘጋጀት ሃሳብ-ለማቅረብ፣ 'የየግል የትምህርት ዕቅድ (Individualized Education Plan (IEP)' ስብሰባን ያደርጋል። ይህ፤ 'ለልዩ ትምህርት የመጀመሪያ የብቁነት ሂደት (initial eligibility process for special education)' - ተብሎ ይጠራል። ስለዚህ-ሂደት የበለጠ መረጃን - ከዚህ በታች ማግኘት ይችላል።

## ለልዩ ትምህርት (Special Education) እና/ወይም ተዛማጅ- አገልግሎቶች ብቁ-መሆን

‘ለልዩ ትምህርት (special education)’ እና/ወይም ‘ለተዛማጅ-የሆኑ አገልግሎቶች (related services)’ ብቁ-ለመሆን፤ ሁለት-ነገሮች እውን-ሆነው መገኘት አለባቸው:

1. በ‘ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ (Individuals with Disabilities Education Act (IDEA)’ በቀረበው-መሠረት፣ ልጃችሁ ጉዳተኝነት (disability) ያለው-መሆን አለበት።
   እና
2. ጉዳተኝነቱ/disability፤ “የልጁን ትምህርታዊ ክንውን-ላይ ጉልህ-በሆነ ሁኔታ ተጽዕኖ የሚፈጥር” መሆን-አለበት (IDEA 300.8(c))
   a. ከፍተኛ-ተጽዕኖ (adverse effect) ያለው የሚለው የሚያመለክተው፤ የልጁ ጉዳተኝነት፣ ከመማር-ሂደታቸው ጋር እክል-የሚፈጥር በሚሆን-ጊዜ ነው። ይህ የሚያካትተው፤ የቀለም-ትምህርት ውጤቶች (academic grades)፣ ልጁ ከአስተማሪዎች እና እኩዮቹ-ጋር እንዴት የእርስ-በርስ ግንኙነት እንደሚያደርግ፣ ልጁ እንዴት እንደሚማር፣ እና ሌሎችንም-ያካትታል።

በ‘IDEA’-ትርጓሜ የተሰጣቸው ጉዳተኝነቶች/disabilities - የሚከተሉት ናቸው:

1. ልዩ-የሆነ የመማር ጉዳተኝነት (Specific learning disability (SLD)፣
2. ሌላ የጤና እክል
3. የኦቲዝም ስፔክትረም እክሎች (Autism spectrum disorder (ASD)
4. ስሜታዊ መረባበሽ/Emotional disturbance
5. የንግግር ወይም የቋንቋ እክል (Speech or Language Impairment)
6. የእይታ እክል (Visual impairment ዐይነ-ስውርነትን - ጨምሮ
7. መስማት-አለመቻል/Deafness
8. መስማት-የተሳነው-ዐይነ-ስውር/Deaf-blindness
9. የመስማት እክል/Hearing impairment
10. የአጥንት ወይም የጡንቻ (Orthopedic) እክል
11. የአዕምሮ-የማገናዘብ ጉዳተኝነት/Intellectual disability
12. አሰቃቂ-የሆነ የአንጎል ጉዳት/Traumatic brain injury
13. በርካታ-የሆኑ ጉዳተኝነቶች (Multiple disabilities)
14. የዕድገት መዘግየት (Developmental delay)* (ይህ ጉዳተኝነት/disability - ዕድሜያቸው 6 እና ከዚያ-በታች ለሆኑ ልጆች ብቻ - ያላቸውን እክሎች-የሚመረምር-ነው)

## የሂደቱ - እርምጃዎች/Steps

የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DC Public Schools (DCPS)፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች ለግምገማው - በደንብ-እንዲያውቁት የተደረገ የጽሁፍ ፈቃድ-መስጫ/informed written consentን ከሰጡ-በኋላ፣ በ60 ቀናቶች ውስጥ - የብቁነት ሂደቱን መጨረስ-አለባት። የዚህ ሂደት ግብ/goal፤ ልጃችሁ - የልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች - ማግኘት-ያስፈልገው እንደሆነ እና እንዳልሆነ መመልከት-ነው። ልጃችሁ ብቁነትን ካገኘ እና ለአገልግሎቶቹ የመጀመሪያው ስምምነት/initial consent for services ከተሰጠ፤ የመጀመሪያው ብቁነት/initial eligibility በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ - ‘አይኢፒ (IEP)’ እና/ወይም የአገልግሎቶች ዕቅድ (Services Plan) እንዲቀርቡ ሃሳብ-ይቀርባል። አገልግሎቶቹ፤ በተገቢው የጊዜ-ገደብ ውስጥ - ይጀምራል።




1. **ወላጅ/አሳዳጊ እና ትምህርት ቤት፣ ስጋቶች ላይ - መወያየት**

   ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት፤ ሁሉም ሰው በአንድ-ገጽ ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣ ይህ እንደ መጀመሪያው እርምጃ/first step ሆኖ የሚበረታታ ነው። ተማሪው፣ ጉዳተኝነት/disability ሊኖረው-የሚችልባቸውን - ማንኛውንም ስጋቶች፣ ትምህርት ቤቱ እና ወላጅ መነጋገር አለባቸው።

2. **መመራት (Referral) ተደርጓል**

   ወላጆች/አሳዳጊ፣ ወይም ልጁን-በደንብ የሚያውቀው-ሰው፤ የልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ወደ dcps.childfind@k12.dc.gov የ‘መምራት (referral) ቅጽን በማስገባት - የመመራት-ሂደቱን ሊያደርግ-ይችላል።

‘መመራት (referral)’ን - የሚከተሉት ሰዎች ሊያስገቡ ይችላሉ:

- ወላጅ/አሳዳጊ
- ልጁ በሚማርበት-ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ስለልጁ በደንብ-የሚያውቅ የትምህርት ቤቱ ተቀጣሪ-ሠራተኛ

- የሕዝብ ድርጅት ውስጥ ተቀጣሪ ሠራተኛ የሆነ - ስለልጁ የሚያውቅ - እንደ ማህበራዊ ሠራተኛ (social worker) ያለ ወይም ከዲሲ የልጅ እና የቤተሰብ አገልግሎቶች ኤጀንሲ (DC's Child and Family Services Agency (CFSA) - ጉዳይ-አስፈፃሚ (case manager)

ዕድሜው ከ6 ዓመት በታች ለሆነ ልጅ፤ ተጨማሪ ሰዎች - መምራቱ (referral)ን ሊያስገቡ-ይችላሉ:

- የሕፃናት-ሐኪሞች (Pediatricians) ወይም ሌላ የሕክምና ባለሞያተኞች
- የዴኬር (Day care) ማዕከሎች
- የማህበረሰብ ድርጅቶች (Community organizations)

ለወላጅ፣ የወላጅ ክንውኖች የደህነት-መብት ጥበቃ/parent procedural safeguards ቅጂ/copy፤ ይሰጣል።

ተማሪው - በዲሲ ውስጥ፣ በግል-ትምህርት ቤት (Private School) ውስጥ ወይም በመኖሪያ-ቤት መማሪያ (Homeschool) ውስጥ የሚማር-ከሆነ፤ ከመመራት ቅጹ (referral form) በተጨማሪ - የሚከተሉት ሰነዶች ያስፈልጋሉ:

- ከትምህርት ቤቱ - የምዝገባ ማረጋገጫ ወይም ከ'OSSE' በመኖሪያ-ቤት ለመማር ፈቃድ-ያገኙበትን ደብዳቤ/Homeschool Authorization Letter
- የነዋሪነት ማረጋገጫ

ሌሎች-የሚመከሩ ሰነዶች - የሚከተሉትን ያካትታል:

- የመስማት እና የዕይታ (Hearing and vision) ምርመራ - በአለፈው-ዓመት ውስጥ የተደረገ
- በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትና አለመገኘት (Attendance) መዝገቦች
- ሪፖርት ካርዶች
- መሠረታዊ የሆኑ የፈተና ውጤቶች (Standardized test scores)
- የሥራ ናሙናዎች (Work samples)

አንድ-ጊዜ መመራቱ/referral ከተቀበሉ በኋላ፣ የማዕከላዊ የሆነ የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድን - ሁሉን ቀደምት-የሆኑ የመረጃ-ስብስብ/dataን - ልጁን በትምህርታዊ አካባቢው ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ ምልከታ-ማድረግን ጨምሮ - ያለውን መረጃ ለመሰብሰብ፣ ከወላጆች እና ከትምህርት ቤቱ ጋር ይሰራሉ። አንድ-ጊዜ የማዕከላዊ የሆነ የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድኑ ሁሉንም ቀደምት-የሆኑ የመረጃ-ስብስብ/dataን መሰብሰብ ካጥናቀቀ በኋላ፣ ጉዳዩ ወደ ጉዳይ-አስፈጻሚው (case manager) የሚሰጥ-ይሆናል።

### 3. የ'Analyzing Existing Data (AED)' ስብሰባ / የምርመራ-ምልከታ (Screening)

የ'AED' ስብሰባውን የጊዜ-ሰሌዳ ለማያዝ - DCPS ያነጋግራችኋል። በስብሰባው ወቅት ላይ - የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድኑ፤ ቀድሞ-የሚገኘውን የመረጃ-ስብስብ (data) ላይ ምልከታ-ያደርግ እና ሌላ ተጨማሪ ግምገማዎች ያስፈልጉ-እንደሆነ ውሳኔ ያደርጋል። በስብሰባው ላይ፣ ወላጅ/አሳዳጊ እና የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድን፤ የሚሳተፉበት ነው። የግል (private) ትምህርት ቤቱ እንዲገኝ-ይጋበዛል፣ ነገር-ግን የመካፈል-ግዴታ የለበትም።

የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድኑ፣ ለግምገማው ዋስትና-የማይሰጥ ከሆነ፤ የወላጅ ክንውኖች የደህነት-መብት ጥበቃ/parent procedural safeguards ቅጂ/copyን፤ ለወላጅ ይሰጣል። በዚህ ሰነድ-ውስጥ፤ አቤቱታን-ለማቅረብ - የወላጅ መብቶች፣ ተጠቅሰዋል። ከውሳኔው እና ከተሰጠው-ምክንያት ጋር-አብሮ ሆኖ፣ 'ቀደም-ብሎ የተፃፈ ማስታወቂያ (Prior Written Notice (PWN)'፣ ለወላጅ የሚሰጠውም-ይሆናል። ሂደቱ፤ እዚህ ሊያልቅ-ይችላል

የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድኑ፣ ለመጀመሪያ ግምገማ (initial evaluation) ዋስትና-የሰጠ መሆኑን ከወሰነ፤ በመቀጠልም - DCPS፣ 'PWN'ን የሚሰጥ እና ወላጅ -በደንብ-እንዲያውቁት የተደረገ የጽሁፍ ፈቃድ-መስጫ/informed written consentን እንዲያቀርቡ-ይጠየቃሉ። አንድ-ጊዜ፣ ከወላጅ 'በደንብ-እንዲያውቁት

የተደረገ የጽሁፍ ፈቃድ-መስጫ/informed written consent'ን ከተቀበሉና-ካገኙ በኋላ፣ የመጀመሪያ ግምገማው (initial evaluation) መቀጠል-ይችላል።

## 4. ተጨማሪ ግምገማዎች

DCPS፤ ለልዩ ትምህርታዊ ነገሮች ዙሪያ-አስፈላጊ-ለሆነው፣ መደረግ-የሚያስፈልገውን ግምገማዎች ያከናውናሉ። ግምገማዎቹ፤ በDCPS አጎራባች (Neighborhood) ትምህርት ቤት ውስጥ ሊከናወኑ-ይችላሉ። 'ቀደም-ብሎ የተፃፈ ማስታወቂያ (Prior Written Notice (PWN)'ው፤ ምን-ዓይነት ግምገማዎችን ለማድረግ፣ በDCPS ሃሳብ-የቀረበባቸውን ዝርዝሮችን ይዞ፣ ለወላጅ ያቀርባል።

ይህ፣ ውሳኔው-ላይ ለመድረስ የቀረቡትን ምክንያቶች የሚያካትት-ይሆናል።

5. **ብቁነት (Eligibility)**

የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድኑ - ልጁ፣ ለልዩ ትምህርት (special education) ብቁነት የለውም ብለው ከወሰኑ፤ ለምን-DCPS የማይቀጥል-እንደሆነ - መሠረታዊ-የሆኑትን ምክንያቶች የሚገልጽ 'PWN'ን ለወላጅ ያቀርባል። ሂደቱ፤ በእዚህ-ላይ ያልቃል።

የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድኑ - ልጁ፣ ለልዩ ትምህርት (special education) ብቁ-ነው ብለው ከወሰኑ፤ ወላጅ - አገልግሎቶቹን-ለማግኘት፣ የመጀመሪያ ስምምነት-መስጫ (initial consent)ን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።

6. **የየግል የትምህርት ዕቅድ (Individualized Education Plan (IEP) - ስብሰባ**

ለአገልግሎቶቹ - የመጀመሪያው ስምምነት (nitial consent) ከተሰጠ፣ ከዚያ-በመቀጠል - በ'አይኢፒ (IEP)'ው ላይ ሃሳብ-ለማቅረብ፣ የ'አይኢፒ (IEP)' ስብሰባ ይደረጋል። 'አይኢፒ (IEP)'ው፣ ልዩ ትምህርት (special education)ን እና ተዛማጅ-የሆኑ አገልግሎቶች (related services)ን - ለልጁ ያቀርባል። የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድን፤ በዚህ ስብሰባ ወቅት-ላይ - ሃሳብ-በቀረበበት 'አይኢፒ (IEP)' ላይ ምልከታ-ያደርጋል። ትምህርት ቤቱ እንዲገኝ-ይጋበዛል፣ ነገር-ግን የመካፈል-ግዴታ የለበትም። 'አይኢፒ (IEP)'ው፣ ልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶችን እና ምደባ/placementን - የሚጠቁም-ይሆናል።

የ'አይኢፒ (IEP)' ቡድኑ፣ የሚከተሉትን ያካትታል:

- ወላጅ/አሳዳጊ
- ልጁ (ተገቢ-ሆኖ ከተገኘ)
- የልዩ ትምህርት (Special education) አስተማሪዎች
- የአጠቃላይ-ትምህርት (General education) አስተማሪዎች
- ተዛማጅ የሆነ አገልግሎት (Related service) ሰጪዎች
- ሌላ የትምህርት ቤቱ ቁልፍ-የሆኑ የሠራተኛ አባላቶች
- ሌሎች ግለሰቦች፤ በወላጅ ወይም በ'DCPS' ፈቃድ-አግኝተው - እንዲገኙ የተደረጉ፤ ስለ ልጁ ዕውቀት ያላቸው ወይም ልዩ ሙያተኝነት ያላቸው፤ የተዛማጅ-የሆኑ አገልግሎቶች (related services) ተቀጣሪ-ሠራተኞች፣ ተገቢ-ሆኖ ከተገኘ/if appropriate

ከስብሰባው በኋላ፣ የተፈረመበትን ስምምነት/consent - ወላጅ እንዲያቀርብ ይጠየቃል። አንድ-ጊዜ የተፈረመበትን - 'አይኢፒ (IEP)' ከተቀበሉ-በኋላ፣ የDCPS ትምህርት ቤት - 'አይኢፒ (IEP)'ውን ማስፈጸም-ይጀምራል።

**በ'አይኢፒ (IEP)' ሂደቱ ውስጥ፣ የወላጅ ሚና**

እንደ ልጃችሁ ወላጅ/አሳዳጊ እንደመሆናችሁ ሁሉ፤ በ'IEP' ቡድኑ ውስጥ፣ በጣም-አስፈላጊ-የሆናችሁ አባላቶች ናችሁ። ከስብሰባው-በኋላ፣ በአምስት (5) የስራ-ቀናቶች ባልበለጠ-ጊዜ ውስጥ፣ የተጠናቀቀውን የ'አይኢፒ (IEP)' ቅጂ/copy - DCPS ለእናንተ-ያቀርባል።

## 'IEP'ዎች - ከሌላ የአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲዎች/Local Education Agencies (LEAs)

ተማሪው፤ DCPS ካልሆነ - ከሌላ 'LEA'፣ 'አይኢፒ (IEP)' ያለው-ከሆነ እና ቤተስቡ - ፍትሃዊነት-ያለው አገልግሎቶች (Equitable Services) ማግኘት-የሚፈልጉ ከሆነ፤ መመራት/referralን ሲያስገቡ፣ አሁን-ያለውን 'አይኢፒ (IEP)' እና ሌላ ማንኛውንም የግምገማ ሪፖርቶች ከDCPS ጋር ማጋራት አለባቸው። ቀድሞውኑ-የሚገኘው የተማሪው 'አይኢፒ (IEP)' - 'ንግግር/Speech'ን የሚያካትት ከሆነ፤ በአሁኑ-ጊዜ ባለው 'አይኢፒ (IEP)' ላይ መሠረት-አድርጎ DCPS - የአገልግሎቶች ዕቅድ (Services Plan)ን መፃፍ-የሚችል፣ እና - አንድ-ጊዜ መመራቱ/referral እና 'አይኢፒ (IEP)'ውን ከተቀበለ-በኋላ - በፍትሃዊነት-ያለው አገልግሎቶች (Equitable Services) አማካኝነት፣ 'ንግግር/Speech'ን ይሰጣል። አንድ-ጊዜ የብቁነት ሂደቱ ከተጠናቀቀ-በኋላ፤ ተማሪው አሁንም-ቢሆን ለንግግር/Speech ብቁ-ሆኖ ከተገኘ፣ አዲስና-የተስተካከለ (updated) -

የአገልግሎቶቹ ዕቅድ/ Services Plan ይፃፋል።

## ዳግም-ግምገማ (Reevaluation)

በልዩ ትምህርት (special education) ውስጥ ብቁነትን ለመቀጠል፤ ቢያንስ በየሦስት (3) ዓመታት አንድ-ጊዜ መወሰን-አለበት። ይህ፣ “ዳግም-ግምገማ/reevaluation” ወይም “የየሦስት-ዓመት ግምገማ/triennial evaluation” - ተብሎ-ይጠራል። የሦስት-ዓመት ግምገማ/triennial evaluation የተሰጣቸው - ለልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች - ብቁነት እንዳላቸው የተለዩ ሁሉም ተማሪዎች፣ በዲሲ ውስጥ፣ በሕዝብ ወይም በግል ትምህርት ቤት የሚማሩም-ቢሆንም ወይም ባይሆኑም፣ ዳግም-ግምገማ (Reevaluation)ው - የወላጅን - በደንብ-እንዲያውቁት የተደረገ የጽሁፍ ፈቃድ-መስጫ/informed written consentን - የሚጠይቅ-ይሆናል። ወላጅ ዳግም-ግምገማ ለማድረግ ካልፈለገ እና ተማሪው በአሁኑ-ጊዜ -በ‘አይኢፒ/IEP’ ወይም በ‘አገልግሎቶች ዕቅድ (Services Plan)’ በኩል አገልግሎቶችን እያገኘ-ከሆነ፤ አገልግሎቶቹ ያበቃሉ። ከሦስት-ዓመት ግምገማ/triennial evaluation የጊዜ-አቀማመጥ ውጪ - ወላጅ/አሳዳጊ - አዲስና-የተስተካከለ (updated) የ‘FAPE’ ማቅረቢያን ለማግኘት የሚፈልጉ-ከሆነ፤ አዲስና-የተስተካከለ አይኢፒ (updated IEP)ን ለማግኘት፣ ወላጅ/አሳዳጊ ይህን ጥያቄ በጽሁፍ ለDCPS.ChildFind@k12.dc.gov በመጠየቅ-ማቅረብ አለባቸው። ከመጪው የትምህርት ዓመት በፊት፣ አዲስና-የተስተካከለ (updated) የ‘FAPE’ ማቅረቢያን ወላጆች-ማግኘት ከፈለጉ፤ ይህን ጥያቄ በጃንዋሪ (January) ወር ውስጥ እንዲያደርጉ-ይበረታታሉ።

## ፍትሃዊነት ያለው አገልግሎቶች (Equitable Services)

ፍትሃዊነት ያለው አገልግሎቶች (Equitable Services)፣ በዲሲ ውስጥ በሚገኝ ካለትርፍ-የሚሰራ የግል-ትምህርት ቤት/nonprofit private school ውስጥ በወላጅ-ምደባ ለሚማሩ ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ናቸው። ተማሪዎች የዲሲ ነዋሪዎች ከሆነ፣ እና ወላጅ - ‘ነፃ ተገቢ-የሆነ የሕዝብ ትምህርት (Free Appropriate Public Education (FAPE)ን ለማግኘት ከጠየቀ፤ ከዚህ-በመቀጠል - ‘አይኢፒ (IEP)’ እንዲሰራ ሃሳብ-ይቀርባል። አንድ ተማሪ፤ የ‘አይኢፒ (IEP)’ አገልግሎታቸውን - በማንኛውም ጊዜ፣ በአካባቢው የDCPS ትምህርት ቤት ውስጥ - ሊያገኝ-ይችላል።

የተሰጠውን ‘አይኢፒ (IEP)’ እና ‘FAPE’ን ቤተሰቡ ካልተቀበለው፣ እና ተማሪው - ለንግግር-ቋንቋ ፓቶሎጂ (Speech Language Pathology) እና/ወይም ኦኩፔሽናል ቴራፒ (Occupational Therapy) ብቁ-ከሆነ፤ ከዚህ-በመቀጠል፣ ፍትሃዊነት ላለው አገልግሎቶች (Equitable Services) - የአገልግሎቶች ዕቅዱ/Services Plan የሚፃፍ እና፣ በ‘አይኢፒ (IEP)’ ስብሰባው ወቅት ላይ የሚቀርብ-ይሆናል። ተማሪው - የዲሲ ነዋሪ ካልሆነ እና ለንግግር-ቋንቋ ፓቶሎጂ (Speech Language Pathology) እና/ወይም ለኦኩፔሽናል ቴራፒ (Occupational Therapy) ብቁነትን-ካገኘ፤ የአገልግሎቶች ዕቅድ (Services Plan) ብቻ የሚፃፍ እና የሚሰጠው-ይሆናል።

እንደ ፍትሃዊነት ያለው አገልግሎቶች (Equitable Services) አንዱ-አካል ሆኖ፣ የ‘ንግግር ቋንቋ ፓቶሎጂ/Speech Language Pathology (የንግግር ቴራፒ/Speech Therapy) እና ኦኩፔሽናል ቴራፒ (Occupational Therapy)’ - በአሁኑ-ጊዜ ይሰጣሉ። ይህ የሚያካትተው፤ ቀጥተኛ አገልግሎቶች የሚሰጥበትን ጊዜ - ቴራፒስቱ/therapist - ከተማሪው ጋር በሚሰሩበት ጊዜ፤ እንዲሁም የማማከሪያ ጊዜ (time for consultation) - ቴራፒስቱ ከአስተማሪ ወይም ከወላጅ ጋር የማረጋገጫ-ውይይትን የሚያካሂዱበትን ጊዜ - ያካትታል። እንደ ፍትሃዊነት ያለው አገልግሎቶች (Equitable Services) አንዱ-አካል ሆኖ፣ የ‘ንግግር ቴራፒ (Speech Therapy) እና ኦኩፔሽናል ቴራፒ (Occupational Therapy)’ ብቻ ይሰጣል።

### ዓመታዊ ስብሰባ

የዓመታዊ የአገልግሎቶች ዕቅድ/Services Plan ስብሰባ፣ በዓመት-አንድ ጊዜ - ስለ ተማሪው የአገልግሎቶች ዕቅድ አዲስና-ማስተካከያ/update ለማድረግ ይካሄዳል። በ‘አገልግሎት ዕቅዶች/Services Plans’ ላይ የሚገኙ-መረጃዎች፣ ከዚህ በታች ይገኛሉ። ወላጆች/አሳዳጊ፤ ከDCPS ወኪል - ጋር እና ከተማሪው የንግግር ቴራፒስት (Speech Therapist) ጋር-በመሆን፣ እንዲካፈሉ ይጠየቃሉ። የግል/private ትምህርት ቤቱ እንዲካፈል ይጋበዛል፣ ነገር ግን በግድ-የሚያስፈልግ አይደለም።

### የአገልግሎቶች ዕቅድ

ተማሪው የዲሲ ነዋሪ ከሆነ፤ ‘አይኢፒ/IEP’ውን ባዘጋጁንት-በእነዚሁ አንድ-ሰዎች፣ ‘የአገልግሎቶች ዕቅድ/Services Plan’ ይዘጋጃል። ‘የአገልግሎቶች ዕቅድ/Services Plan’ የሚገልጸው፤ በDCPS የተሰጠው ፍትሃዊነት (Equitable) ያለው

አገልግሎቶች፣ በግል-ትምህርት ቤቱ ውስጥ መተግበር-ያለበት መሆኑን - ይገልፃል። በአሁኑ-ጊዜ፤ እነዚህ አገልግሎቶች - የ'ንግግር ቴራፒ/Speech Therapy እና ኦኩፔሽናል/Occupational Therapy)'ን ያካትታል። 'የአገልግሎቶች ዕቅድ/Services Plan'፤ ስለተማሪ በአሁኑ-ጊዜ ያለውን የክንውን-ደረጃዎች (present levels of performance) እና ዓመታዊ ግቦችን - የሚገልጽ መረጃዎችን አካትቶ-የያዘ ይሆናል።

## ፍትሃዊነት(Equitable) ያለው አገልግሎቶች ማግኘት

የ'አገልግሎቶች ዕቅዱ (Services Plan)' በስራ-ላይ የሚውለው፤ አንድ-ጊዜ ወላጅ/አሳዳጊ የተፈረመውን የ'አገልግሎቶች ዕቅድ (Services Plan)' ወደ DCPS መልሰ-ካስገባ በኋላ - የአገልግሎቶቹ አፈፃጸም መተግበር-ይጀመራል።

አንድ-ጊዜ የተፈረመው ‘የአገልግሎቶች ዕቅድ/Services Plan’ን ከተቀበሉ-በኋላ፣ የቴራፒ የጊዜ-ሰሌዳ (therapy schedule) አድርጎ-ለማጠናቀቅ እንዲችል፣ የግል ትምህርት ቤቱ/private schoolን ያነጋግሩታል። አንድ-ጊዜ የጊዜ-ሰሌዳው ከተስተካከለ በኋላ፣ በኢሜል አማካኝነት - ከቴራፒስቱ/therapist የእንኳን-ደህና መጣችሁ ደብዳቤን ወላጅ-የሚያገኝ እና አገልግሎቶቹ መሰጠት ይጀምራሉ። ለአገልግሎቶች ዕቅድ (Services Plan) ዓመታዊ-ስብሰባ እና ለየሦስት-ዓመቱ ዳግም-ግምገማ (Triennial re-evaluation)፤ ወላጅ እና ትምህርት ቤቱ፣ በDCPS የማሳወቂያ-ግንኙነት (contact) ይደረጋሉ።

በእያንዳንዱ የትምህርት አዓመት - የፍትሃዊነት ያለው-አገልግሎቶች (Equitable Services) እንዲቀጥሉ-ለማድረግ፣ ወላጅ ስምምነት መስጠት እንዳለባቸው፤ እባካችሁ አስታውሱ። በየ-እያንዳዱ የፀደይ (Spring) ወቅት-ላይ - በአሁኑ-ጊዜ ፍትሃዊነት ያለው አገልግሎቶች (Equitable Services)ን እያገኙ ለሚገኙ ተማሪዎች-ወላጆች፤ ለመጪው የትምህርት ዓመት - የተማሪውን ትምህርት ቤት እንዲያጋሩ እና ተማሪው በዲሲ የግል ትምህርት ቤት ውስጥ የሚቆይ-ከሆነ - አገልግሎቱን-በማግኘት መቀጠል የሚፈልጉና-የማይፈልጉ መሆናቸውን - ወላጆች እንዲያረጋግጡ፤ DCPS አግኝቶ-ያነጋግራቸዋል። ይህን ሞልቶ አለማጠናቀቅ፣ የአገልግሎቶች መቋረጥን ሊያስከትል ይችላል።

ኤሊዛቤት ስታል (Elisabeth Staal)፣ የ‘CIEP’ ቡድን አስተባባሪ፤ ፍትሃዊነት (Equitable) ያለው አገልግሎቶችን - ለሚያገኙ ተማሪዎች፣ ጉዳይ አስፈፃሚ (case manager) ናቸው። ማንኛውም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሏችሁ፤ እባካችሁን በelisabeth.staal@k12.dc.gov አግኝታችሁ ልታነጋግሯቸው-ትችላላችሁ።